# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፦ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ሐምሌ 14 ቀን 2004 ዓ.ም**

**በአወሊያ 18 ሰዎች መገደላቸውን የአይን እማኞች አጋለጡ፤**

**ቀይ ቆብ ያጠለቀው የአጋዚ ጦር አወሊያ መስጊድ ገብቶ በእሩምታ መግደሉ ተጋለጠ፤**

**የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች በሙሉ ታፍሰው ማዕከላዊ ታሰሩ፤**

ከስምንት ወራት በፊት ጀምሮ ሙስሊሙ ህዝብ ላቀረበው የመብት ጥያቄ ተገቢ የሆነ መልስ በመስጠት ፈንታ የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ችግሩን አባብሶ ሰው የመግደልና የማሰር እርምጃ መውሰድ መጀመሩን ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋበያችን የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

የወያኔ ቡድን ሰላማዊና ህጋዊ የመብት ጥያቄ የሚያነሱትን ዜጎች በሽብርተኝነት ስም እየፈረጀ ለእስር ከመዳረጉም በላይ በእብሪት እና በማን አለብኝነት በዜጎች ላይ የሚወስደውን እርምጃ አስፋፍቶ በመቀጠል ሰሞኑን በአወሊያ መስጊድ ከ18 ሰዎች በላይ የገደለ መሆኑ ታውቋዋል፡፡

በሀይማኖታችን ውስጥ ገብታችሁ አተፈትፍቱ እራሳችን በራሳችን ችግሮችን እየቀረፍን የእምነት ተግባሮቻችንን እናከናውናለን ባሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ ወያኔ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ለወራት ሲያደርግ ከመሰነበቱም በተጨማሪ ዐርብ ዕለት ሐምሌ 6 ቀን 2004 ዓ.ም ምሽት 5 ሰዓት ላይ በአወሊያ መስጊድ ውስጥ በተገኙ የእምነቱ አማኞች እና አባቶች ላይ በአልሞ ተኩዋሽ የአጋዚ ቅልብ ጦር አማከይነት 18 ሰዎች እንዲገደሉ ማደረጉን በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞችን ያነጋገረው የተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ሙስሊሙን ይወክላሉ የተባሉትን ጊዜያዊ ኮሚቲ አባላት በማሳደድ የተጀመረው ግጭት ወደ ሰው መግደል የተሸጋገረ መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ የእምነቱ አባቶች ዓርብ ዕለት በአወሊያና በአንዋር መስጊድ ውስጥ የተፈጸመው አሳዛኝ እና ዘግናኝ ጭፍጨፋ ጣሊያን በስድስት ከሎ ከወሰደው የጅምላ ጭፍጨፋ ጋር ተመሳሳይ መሆኑንን እንባ እየተናነቃቸው ሲናገሩ መደመጣቸው ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

ዓርብ ዕለት ከሌሊቱ 5 ሰዓት ጀምሮ በተከፈተው የእሩምታ ተኩስ ከተገደሉት እና ከቆሰሉት ሰዎች በተጨማሪ በቦታው ላይ የነበሩትን አፍሰው ወደ ጦላይ የጦር ማሰልጠኛ ካምፕ ሌሊቱን ጭነው መውሰዳቸውን የጠቀመው የዘጋቢያችን ሪፖርት በሌሎችም መስጊዶች  የተገኙትን ምዕመኖችንም አፍሰው መውሰዳቸውን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

በአወሊያ መስጊድ የተጀመረው ይሄው ወያኔን የመቃወም እርምጃ በአንዲት ሰዓት እና ደቂቃ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባ ባሉ መስጊዶች በሙሉ የተከናወነ ሲሆን በተለይ በትልቁ አንዋር መስጊድ እና ቁራ በሚገኘው መስጊድ እጅግ ህዝብን የሳበ ንቅናቄ በማድረጋቸው ህዝበ ክርስቲያኑ ጭምር ተቀላቅሎ በተቃውሞው ተሳታፊ የነበረ መሆኑም ታውቋዋል፡፡

ከዚሁ አፈና በተጨማሪ ህዝበ ሙስሊሙን በአንድነት ለማቀራረብ እና ለማስተሳሰር የሚረዳውን ሰደቃ ፕሮግራም ለማድረግ ከ800 ሺህ ብር በላይ ከህዝቡ ተዋጥቶ በተለያዩ መስጊዶቸ ውስጥ በሬዎች ታርዶ በመዘጋጀት ላይ እንዳለ የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ እና አጋዚ ጦር የተሰራውን ምግብ ወደ ቆሻሻ ገንዳ ከመድፋታቸውም በላይ በቁም ሳይታረዱ የነበሩ   በሬዎችን ገሚሱን በጥይት ገድለው ሲጥሉ ገሚሶቹን ደግሞ በመኪና ጭነው መውሰዳቸውንም ከዘጋቢያችን ያገነኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ዓርብ ሐምሌ 6 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 1 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ በሁሉም መስጊዶች መትረየስ በተጠመዱ ፓትሮሎች ጭምር ጥብቅ ጥበቃ ሲያደረግ የዋለው የወያኔ ቡድን ሲቪል የለበሱ ክትትል ፖሊሶች እና ደህንነቶችን በየመስጊዱ ገብተው እንዲሰልሉ በማድረጉ  ብጥብጡ ሊነሳ እንደቻለ የጠቀመው የዘገቢያችን ሪፖርት ይህንኑ በመቃወም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መልኩ በየመስጊዱ ውስጥ ሌሊቱን በጾሎት ለማሳለፍ በወሰዱት እርምጃ ወያኔ አስከፊና አሳዛኝ ብሎም ዘግናኝ እርምጃ ሲፈጽም ማደሩን ከዘጋቢያችን ያገኘውን ሪፖርት ገልጾዋል፡፡

ቅዳሜ ሐምሌ 7 ቀን 2004 ዓ.ም በተለይ በአንዋር መስጊድ ዙሪያ የፈሰሰው የፌዴራል ፖሊስ ብዛት አስደንጋጭ የነበረ ሲሆን በዚህ እርምጃ የተበሳጩት የመርካቶ አካባቢ ነጋዴዎች ሱቆቻቸውን ዘግተው እስከ ማክሰኞ ዕለት ድረስ ሳይከፍቱ እንደቆዩም ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡

በየመስጊዱ በሙስሊሞች ወገኖቹ ላይ እርምጃ ሲወሰድ የተመለከተው ክርስቲያኑ በመተባበር ለሙስሊም ወገኖቹ ለከለላና መጠለያ ሲሰጥ ከማደሩም በተጨማሪ በተቃውሞው ላይም ተቀላቅሎ እንደነበር ማወቅ ተችሏል፡፡  በመርካቶ አካባቢ ሱቅ ያላቸው ክርስቲያኖችም በአድማው በመሳተፍ እስከ ማክሰኞ ሐምሌ 10 ቀን 2004 ዓ.ም  ድረስ ሱቃቸውን ዘግተው እንደነበር ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ችለናል፡፡

ሰሞኑንም የሙስሊሙን ህዝብ ጥያቄ ለማዳፈን እና ጨርሶ ለማጥፋት ሲል የወያኔ ቡድን በሚሊዮን የሚቆጠር ብር መድቦ ከዞን ከተማ እስከ ወረዳ ድረስ በመበተን የተቃውሞ ሰልፍ አደባባይ እንዲወጡ ማድረጉም ታውቆዋል፡፡

ከከሚሴ የጀመረው ይሄው አዲስ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ አዲስ አበባን ሳይጨምር ሌሎች ከተሞች ላይ በገንዘብ ኃይል እየተበተነ ከመሆኑም በላይ በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ

የማይገኝ ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ ሽብርተኛ ተብሎ እንደሚፈረጅ በመገለጹ ህዝቡ በግዴታ እየወጣ መሆኑን ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ዘገባ ገልጸዋል።

በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ደግሞ ዑላማዎች ናቸው የተባሉ የእምነቱ ተከታይ አባቶች በማስፈራሪያና በገንዘብ ድለላ ተደርጎላቸው የሙስሊም መፍትሔ አፈላለጊ ተብለው በሙሊሙ የተመረጡትን እንዲያወግዙ መደረጉንም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማስተማር ስራ ላይ ባሉ ሙስሊም ምሁራኖች እና ሌሎችም ወገኖች ሰሞኑን ባስተላለፉት ጥሪ መሰረት ወያኔ በየግዜው የሚወስዳቸው አሰልቺና ተዓማኒነት የጎደላቸው እርምጃዎች ህዝቡን ያማረሩ ከመሆኑም በላይ ግዜው ያለፈበት ርካሽ የፖለቲካ ሽፋን በመሆኑ ሊቆም ይገባል ሰሉም ገልፀዋል።

ሰሞኑን በሙስሊሙ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ሰቆቃና የተወሰደው እርምጃ ፈሩን የሳተና ለጥያቄው አግባብ ያልሆነ መልስ በመሆኑ የወያኔ ባለስልጣናት በትንሽ በትልቁ ዝም ብለው እየደነበሩ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ አርቀው ሊያስቡ ግድ ይላቸዋል ያሉት እነዚሁ ምሁራኖች በአወሊያና በሌሎችም መስጊዶች ታፍሰው የታሰሩ ዜጎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር ሊፈቱ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

የብጥብጡና የግጭቱ መንስዔ ዋነኛው ምክንያት የሆነው የወያኔ ቡድን የራሴ ናቸው የሚላቸውን ካድሬዎች በሙስሊሙ ላይ ሊያስቀምጥ በመሆኑና ይሄንኑ በመቃወም ምርጫው ፍትሀዊ እንዲሆንና በቀበሌ ሳይሆን በየመስጊዱ ብቻ መደረግ አለበት በማለት ላነሱት ጥያቄ አግባብ ያለው መልስ ከመስጠት ይልቅ በጥይት እና በዱላ መግደልና መደብደቡ ነገሮቹን ሁሉ ውስብስብ እና አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ገልፀው ይህንን በአፋጣኝ የእርምት እርምጃ ካልወሰደ በመጪው ጥቂት ግዜ የሚፈጠረው አደጋ የከፋ ነው ሲሉም ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል።

በቀጣዩ ሳምንት የታላቁ ረመዳን ጾም የሚጀመርበት ወቅት በመሆኑ ህዝበ ሙስሊሙ በሰላምና በነጻነት ብሎም በተረጋጋ ሁኔታ ጾሙን እንዲያከናውንና አምላኩን እነዲያመልክ በአሁኑ ሰዓት በየመስጊዱ በራፍ ላይ ተኮልኩለው የሚገኙት ፖሊሶች መነሳት አለባቸው ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

በተያያዘ ዜና እሁድ ሐምሌ 8 ቀን 2004 ዓ.ም በታላቁ አንዋር መስጊድ በተዘጋጀው የአንድነት እና ሰደቃ ፕሮግራም ላይ ሊገኙ በተጉዋዙት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች ላይ ደህንነቶች ሊያደርጉት የነበረው እገታ እና አፈና ሊከሽፍ እንደቻለ ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የተገኘው ጥቆማ አጋለጠ።

ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ተመርጠው የተሾሙት የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ሰብሳቢውን ኡስታዝ አቡበከርን ጨምሮ አምስት አመራሮች ፕሮግራሙን ለማስጀመር ወደ መስጊድ በመጉዋዝ ላይ እንዳሉ የደህንነት መኪና የሆነች ቶዮታ ኮሮላ መንገድ ዘግታ ደህንነቶች የወረዱና እገታ የፈጸሙባቸው ሲሆን ይህንኑ የተረዱት የኮሚቴ አባሎች በፍጥነት መኪናቸውን አቅጣጫ በመቀየር ከእገታው

ሊያመልጡ እንደቻሉ ከደረሰን የምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡እነዚሁ የሙስሊም መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቲ አባሎች ድንገት ሐሙስ ዕለት ከያሉበት ታፍሰው ማዕከላዊ ምርመራ ጭለማ እስር ቤት ውስጥ መታሰራቸው ታወቁዋል፡፡

ሐሙስ ሐምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ገሚሱን ከየቤታቸው ሌሎቹንም ከያሉበት ሰብስበው በደህንነት እና በልዩ ክትትሎች ለቅመው ማዕከላዊ ምርመራ ያጎሩዋቸው መሆኑ ሲታወቅ ቀዝቃዛ ውሀ በተሞላ በርሜል ውስጥ ለረዥም ሰዓት ከነልብሳቸው አቆይተዋቸዋል የሚል ዜናም ተሰምተዋል፡፡

ሙስሊሙ ምርጫው እስኪፈጸም ድረስ ይወክሉኛል ብሎ የመረጣቸው እነዚሁ የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላለጊ ኮሚቲ ሰብሳቢውነ ኡስታዝ አቡበከር አህመድን፤ በዳዒ ካሚል ሸምሱ፤ኡስታዝ አህመዲን ጀበል፤ አህመድ ሙስጠፋ እና አቶ አክመል ነጋሽ የሚባሉ እንደሚገኙበት ታውቁዋል፡፡

አርብ ሐምሌ 13 ቀንና ቅዳሜ ሐምሌ 15 ቀን በአዲስ አበባና በሌሎች ቦታዎች ህዝበ ሙስሊሙ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ያደርጋል ከሚል ስጋት ቁጥሩ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የወያኔ ወታደር በየመስጊዱ በመሰማራታቸውና የሚወጣውንና የሚገባውን ለመፈተሽ በ ሚያደርጉት ሙከራ ውጥረቱን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሱት መሆኑ ታውቀዋል፡፡